የካቲት 15, 1998

<u>ለአስቸኳይ ስርጭት</u>

<u>ጉዳዩ፡</u> ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ደኢሕዴህ) አመራር ጋር የወቅቱን የኢትዮጵያ ሁኔታ አስመልክተን ያደረግነውን የደብዳቤ ምልልስና ያገኘነውን መልስ ስለማሳወቅ፤

በሰሜን አሜሪካ የምንኖር ጉዳዩ ያሳሰበን የደኢሕዴህ አባላትና ድጋፊዎች ከግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስና የደኢሕዴህ አመራር ሊወስዳቸው ስለሚገባቸው ዕርምጃዎች ፤ እንዲሁም የሕብረቱ አመራር ግልፅነት በጎደለውና ከፋፋይ በሆነ መልኩ "በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት" (ፓርላማ) ስለመሳተፉ ጉዳይና ከዚህም ጋር ተያይዞ ደኢሕዴህ የደረሰበት ደረጃ አሳሰቦን ዕርስ በርሳችን ብዙ ውይይቶችን ከማድረጋችንም በላይ በደኢሕዴህ ሊ/መንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ በኩል ከድርጅቱ ማዕከላዊ አመራር (committee) ጋር የተለያዩ የደብዳቤና ፤ የስልክ ምልልሶችንና ውይይቶችን አድርገናል።

እኛ ጉዳዩ ያሳሰበን የደኢሕዴህ አባላትና ድጋፊዎች ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በሀገሪቱ የፖለቲካ ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ተፈጥሮአዊና አግባባዊ ድርሻ ማበርከት ይገባቸዋል ብለን እናምናለን። እንዲሁም የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያካሄዱት ትግል ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ለዴሞክራሲ ፤ ለሰላምና ፍትህ ከሚያካሄዱት ትግል ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት እናምናለን። ከዚህ ዕምነት ተነስተን ዕርስ በርሳችን ብዙ ውይይቶችን ከደረግን በኋላ ለደቡብ ህብረት አመራር ቀጥሎ የተመለከቱትን ጉዳዮች በጥቅምት ወር ለፓርላማው በጽሑፍና በአካል እንዲያቀርቡ ፤ ፓርላማውም ተወያይቶ ውሳኔ እንዲያስተላልፍና አስፈፃሚ የመንግሥት አካል ደግም በተግባር እንዲተረጉም ብርቱ ጥረት እንዲያደርጉ ጥያቄ አቅርበን ነበር።

1. ሁሉም የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች፤ አባላት ደጋፊዎችና የሕዝብ ተመራጮች ከታሰሩበት ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱ ፤ ታፍነው የተወሰዱ ግለሰቦች ለቤተሰቦቻቸው ፤ በአስቸኳይ እንዲመለሱ ፤ የተዘጉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጽ/ቤቶች እንዲከፈቱና የተወሰዱባቸውም ንብረቶችና ሰነዶች በአስቸኳይ እንዲመለሱ፤
2. በሕዝብ ድምፅ ተመርጠው ወደ ፓርላማ ካልገቡ ተወካዮች በህገወጥነት የተወሰደው ከክስ ነፃ የመሆን መብት በአስቸኳይ እንዲመለስላቸው፤
3. በሕገ-መንግስቱ ለዜጎች የተፈቀዱ የመሰብሰብ ፤ የመናገር ፤ የመጻፍ ፤ የተቃውሞ ሠልፍ የመውጣት ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፤
4. በመስከረም ወር 1998 ተጀምሮ በኢሕአዴግ ግትርነት የተቋረጠው የሶስትዮሽ ድርድር አስቸኳይ እንዲቀጥል፤

5. ከዚህ በላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች አሉታዊ መልስ ከተሰጠና ጥያቄዎቹ በቀረቡ በሰባት ቀናት ውስጥ ጨርሶውኑ መልስ ከተነፈጋችሁ ደኢሕዴህ ከፓርላማ ራሱን ለማግለል የሚገደድ መሆኑን በማያሻማ መልክ ማሳወቅ እንደሚገባው፤

የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጥያቄዎቻችንን በጥሞና መመልከቱንና በአጭር ጊዜ ውስጥም ምላሽ መስጠቱን ብንገነዘብም ፤ ቡድናችን ከማዕከላዊ ኮሚቴው የተሰጠው መልስ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኘው እንደገና ለብዙ ሰዓታት የቆየ ውይይት በስልክ አካሂዶ አመራሩ ጥያቄዎቻችንን እንደገና እንዲመለከተው ለማሳሳብ ሁለተኛ ደብዳቤ እንዲላክ ወሰነ። በዚህም ውሳኔ መሠረት የ15 ሰዎች የስም ዝርዝር ታክሎበት ሁለተኛ ደብዳቤ ተጽፎ ተላከ። በዚህ ደብዳቤ ስማቸው በተዘረዘረው ግለሰቦች ውስጥ ወደ ባዕድ ሀገር ሳይወጡ በፊት የደኢሕዴህ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩና አሁንም ድርጅቱን ወክለው የሚንቀሳቀሱ ፤ እንዲሁም ደኢሕዴህንና የድርጅቱን መሪ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስን ድርጅቱ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ በመርዳት ላይ የሚገኙ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ይገኙበታል።

ዶ/ር በየነ ጴጥሮስና ጓደቻቸው ይህ ሁለተኛ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ገልጸውልን ፤ ነገር ግን የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጥያቄዎቻችንን አጀንዳ ይዞ እንድማይወያይበት ገለጹልን ። ለዚህም የተሰጠን ምክንያት ደብዳቤው ላይ ስማቸው ተዘርዝሮ ያሉ ግለሰቦች በአካል ፊርማ ያለማስቀመጣቸው ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ቀጣይና ተከታታይ ግንኙነቶችን ብናደርግም ደብዳቤውን ዶ/ር በየነ ጴጥሮስና ጓደቻቸው ማዕቀብ አድርገዉበተ ይገኛሉ። ይህ ለደብዳቤያችን ፊርማ መጠየቁ ከዚህ በፊት ያልተለመደ አሠራር ከመሆኑም በላይ ጥያቄዎቻችንን አፍኖ ማቆያ ዘዴ መሆኑን ተገንዝበናል። ከዚህም በላይ በቀረብናቸው ጉዳዮች ዙሪያ የአመራሩ የተሳሳተ ፖለቲካዊ አካሄድ ለደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ስለወሰድንና የደቡብ ሕዝባችንን ትግል መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተያያዘው ወሳኝ ትግል አጋርነት የሚነጥለው እርምጃ ይሆናል ብለን ስለሠጋን ሁለተኛውን ደብዳቤ ከዚህ ማስታውሻ ጋር አያይዘን ሕዝባችን በግልፅ እንዲያውቀው አድርገናል።

በዚህ አጋጣሚ የዚህ ቡድን አካላት እንዲታውቅልን የምንሻው ሌላው ጉዳይ የደቡብ ሕዝቦች ለዕድገት ፤ ለዴሞክራሲ ፤ ለፍትህና ለህግ የበላይነት የሚያድርጉትን ትግል በቀጣይነት መደገፋችንን እንድምንቀጥል ነው።

**ጉዳዩ ያሳሰበን በሰሜን አሜሪካ የምንኖር የድርጅቱ አባሎችና ደጋፊዎች**

ታህሣሥ 7 1998

በዶ/ር በየነ ጴጥሮስ አማካይነት ለደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች
ዴሞክራሲያዊ ሕብረት ማዕከላዊ ኮሚቴ (ደ.ኢ.ሕ.ዲ.ሕ)
ፖ.ሣ.ቁ. 30751
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

የተከበራችሁ የኮሚቴ አባሎች፡

ላቀረብንላችሁ ጥያቄዎች በተሰጡን መልሶች ለመነጋገር ሁለት የቴሌፎን ስብሰባዎችን አካሄደናል፡ በሁለተኛው ስብሰባችንም ሀያ አራት ሰዎች የተሳተፉበት ሲሆን ሁለት ሰዓታት የወሰደ የጋለ ውይይት የተካሄደበትም ነበር። የውይይት ቡድናችን ከነዚህ መነሻ ሃሳቦችና ውይይቶች በመነሣት የሚከተሉትን ግንዛቤዎችና የተግባር ነጥቦችን አሳልፏል።

1. ቡድናችን የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጥያቄዎቻችንን በጥሞና መመልከቱንና ሙሉ ትኩረትም ሰጥቶ መነጋገሩን ተግንዝቦታል።

2. የደብዳቤችን ዋናው መንፈስ የነበረው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት አመራርና የምክር ቤቱ ተመራጭ አባላት ባገሪቱ ውስጥ ለዴሞክራሲና ፍትህ በመደረግ ላይ ባለው ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ኢንዲሳተፉና የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ምክር ቤቱን ለቅቀው እንዲወጡ ለመጠየቅ ነበር። ለቡድናችን ቀደም ሲል ከማዕከላዊ ኮሚቴ የተሰጠው መልስ የሚያሳየው ጥያቄዎቻችን ተቀባይነት እንዳላገኙ ነው። ከዚህም በላይ የተገነዘብነው ቀደም ሲል የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወደ ምክር ቤቱ ለመግባት የወሰነውን ውሳኔ ለማጽደቅ የተጠራው የማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ የተደረገው ይህ የውይይት ቡድናችን ጥያቄዎቹን ለድርጅቱ ካቀረባቸው በኋላ ነበር።

3. ይህ ቡድን ጥያቄዎቻችንን ላላመቀበላችሁ የተሰጡትን ምክንያቶች አጥጋቢ ናቸው ብሎ አይቀበልም። በተጨማሪም የህብረቱ አመራር ባገሪቱ ውስጥ ሕዝቡም ሆነ ድርጅቱ በየዕለቱ ስለሚገጥማቸው ዝርዝር ሁኔታዎች ከኛ የተሻለ ግንዛቤ ይኖረዋል ብንልም ፤ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ስላለው የፖሊቲካ ሁኔታ ፣ መንግስት ስለሚወስዳቸው ፀረ-ሕዝብ እርምጃዎችና ህዝቡም ስለሚወስዳችው የመቋቋም እርምጃዎችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች የአደባባይ ሚስጢር ናቸው። ይህም ማለት ያገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በማወቁ ረገድ በዚህ ቡድንና በድርጅቱ አመራር መካከል ብዙ ልዩነት ይኖራል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል።

4. በደብዳቤው ላይ በምክር ቤቱ መቆየት ያለመቆየታችሁ የሚወሰነው በውስጡ ሆናችሁ በሚከሰቱ ከሥራችሁ ጋር ግንኙነት ባላቸው ክስተቶች ይሆናል ተብሏል። ይህም ማለት በተሳትፏችሁ አመችነትና በትግላችሁ ውጤታማነት ይወሰናል ማለት ነው። ሁኔታው የማያስራ ሁኖ ካገላገኛችሁትም ለቃችሁ እንደምትወጡ ጠቅሳችኋል። ይሁን እንጂ በዚህ

አንድን ሃሳብ በአጀንዳ ለማስያዝ ሃምሣ አንድ በመቶ (51%) ድምፅ እንዲያስፈልግ በተደረገበት ምክር ቤት ውስጥ ገብቶ መሳተፍ ፈይዳ ይኖረዋል ብሎ ይህ ቡድን አያምንም። እንዲያውም የተቃዋሚዎች በዚህ ጉልበትንና ጭቆናን መሣሪያው በማድረግ ስልጣን ላይ ለመቆየት በሚፈልገው ስርዓት ቁጥጥር ስር ባለዉና በሕዝቡም እንደ ሕገወጥ በተቆጠረው ምክር ቤት ውስጥ ገብቶ መሳተፍ የሥርኣቱ መጠቀሚያ ተደርጋችሁ እንድትታዩ ያደርጋቸኋል ብለን እናምናለን።

5. የደቡብ ሕብረት በድርጅታዊ አሰራሩም ሆነ በመረሐ-ግብሩ ዴሞክራሲዊ ድርጅት ነው ብለን እናምናለን። ይሁን እንጂ የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወደ ምክር ቤቱ ለመግባት የወሰነው ዉሳኔና አገባቡም ከሕዝቡ ግልጽ ግንዛቤ የተሰወረና ከፋፋይነት የነበረበት እንደሆነ ይህ ቡድን ያምናል።

6. የደቡብ ሕብረት መሪዎች ወደ ምክር ቤት ለመግባት ያሳለፉት ዉሳኔ በሳል የፖለቲካ እርምጃ ነው ብልው ያምናሉ። የውይይት ቡድናችን ግን የዚህን እርምጃ በሳልነትና ውጤቶቹንም ገና ያላያቸው ከመሆኑም በላይ በቅርቡ በምክር ቤቱ አሰራር ላይ ያላስፈላጊ ገደቦችን የጫነውን ፤ የምክር ቤቱን አባሎች መብት የገፈፈውን ፤ በሕዝብ ምርጫ ወድቀው በተሰናበቱት የቀድሞ አባላት የተደነገገውን የምክር ቤቱን አዲሱን የአሠራር ደንብ መቀልበስ ባልተቻለበትና በቅርቡም ተቀጣጥሎ በነበረው ሕዝባዊ ቁጣ ሳቢያ የታሰሩትን የፖሊቲካ እስረኞች ለማስለቀቅ መንግስትን ቃል ለማስገባት ባልተቻለበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። ይልቁንስ የደቡብ ሕብረት መሪዎች ማድረግ ያለባቸው ከቅንጅት ጋር የተግባር አንድነት በመፍጠር መሪዎቻቸው የሚፈቱበትንና የተቃዋሚዎችም ጥያቄዎች ፤ ለምሳሌ ብሔራዊ የአንድነት መንግሥትንና ነጻ የምርጫ ቦርድ መመስረትን የመሰሉ ጥያቄዎች የሚመለሱበትን መንገዶች መፈለግ ይኖርበታል።

7. ይህ ቡድን እነዚህን ውይይቶች የጀመረበት ሕዝቡ ለዴሞክራሲና ለሕግ የበላይነት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ መንግሥት እየወሰደ ያለዉን እርምጃና ሌሎችንም ከደቡብ ሕብረት ጋር ግንኙነት ባላቸዉ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ነበር። ስለሆነም በደቡብ ሕብረት አመራረና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት መካከል ያለው የወቅቱ ችግር ከአመራሩ ጋር ስናደርጋቸው ከነበሩት ምልልስ እበይት ጉዳዮች አንዱ አልነበረም። ይህ ቡድን ድርጅቱንና የደቡብን ሕዝብ ለዓመታት ሲደግፉ የነበሩና በኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችም መካክል የነበረዉንና አሁንም ያለውን አወዛጋቢ ግንኙንት ጠንቅቀው የሚያወቁ ግለሰቦች የሚገኙበት ነው። ስለዚህም ከቡድኑ አባሎች መካከል አንዳንዶቹ በድቡብ ሕብረት ውስጥ በመስግሰግ የሌሎችን ፖሊቲካ ቡድኖች ጥቅም ለማስከበር ይሞክራሉ የሚባለው አባባል መሰረተ-ቢስ መሆኑን ልናስገነዝብ እንፈልጋልን።

8. በዚህ አጋጣሚ ልናስገነዝብ የምንፈልገው ሌላ ጉዳይ የድቡብ ሕዝቦች እንቅስቃሴ አባሎችና ደጋፊዎች ሚና የገንዝብ እርዳታ በመስጠት ላይ ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነና ድርጅቱንና እንቅስቃሴዉን በሚገጥሙ የታክቲክና የስትራተጂ ጉዳዮችም ሁሉ ሃሳብ መስጠትን ማጠቃለል እንዳለበት ነው። ስለሆነም ይህ ቡድን የደቡብ ሕዝቦች ትግል ከመላ እትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እጅ ለእጅ ተያይዞ መሄድ እንዳለበት አጥብቆ ያምናል።

በዚህ ባገሪቱ ወሳኝ በሆነው የታሪክ ውቅት ሕዝባዊ ድርጅቶች ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል ዉስጥ ታላቅ ሚና እንዳላችውም እንረዳልን።

9. ቀደም ሲል ያቀረብንላችሁ ጥያቄዎች ባለመመለሳቸውና  ላለመመለሳቸውም የተሰጡን ምክንያቶች በቂ ሆነው ስላላገኘናቸው የሕብረቱ አመራር ጉዳዩን እንደገና እንዲመለከተውና አቋሙንም ቀይሮ ከላይ በቁጥር 2 በግልፅ የተቀመጠዉን ሃሳባችንን እንዲቀበል እንደገና እንጠይቃለን። ለነዚህ ጥያቅዎቻችን መልስ በሶስት ሳምንታት ውስጥ ለመሰጠት ብትችሉ ምስጋናችን ክፍ ያለ ይሆናል። ምናልባትም በምክር ቤቱ መቆየቱን የምትቀጥሉ ከሆነ ዉሳኔአችሁ በሚያስከትለው ጉዳትም ሆነ በሚያስገኘው ጥቅም ላይ ከመረጣችሁ  ሕዝብ ጋር ዉይይት እንዲደረግበት መድረክ መክፈት እንደሚያስፈልግም በዚህ አጋጣሚ ለማንሳት እንወዳለን።

10. በመሠረቱ የድርጅቱ አመራር ቀደም ሲል የወሰደውን አቋም ይለዉጣል የሚል ፅኑ እምነት አለን። ይህ ካልሆነ ይህ የተሣሣተ አካሄድ ለዓመታት የተደከመበትን የደቡብ ሕዝቦች የትግል እንቅስቃሴ ከትክክለኛ የትግል ጎዳና ከማስወጣቱም በላይ የደቡብ ሕዝባችንን ትግል መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተያያዘው ወሳኝ ትግል አጋርነት የሚነጥለው እርምጃ ይሆናል። አሁን ነገሮች በሚገኙበት ሁኔታ እኛ (ጉዳዩ ያሳሰበን ቡድን) ራሳችንን ከዚህ ከተሳሳተ የሕብረቱ አመራር ስልት ከማግለል የተሻለ ምርጨ የለንም። ይሁን እንጂ የደቡብ ሕዝቦች ለዴሞክራሲ የሚያድርጉትን ትግል መደገፋችንን እንድምንቀጥል እናረጋግጣለን።

ጉዳዩ ያሳሰበን በሰሜን አሜሪካ የምንኖር የድርጅቱ አባሎችና ደጋፊዎች